# “ፍቅርና ሰላም ከያዙ ሁሌም ደስተኝነት” ከጌጀ

በሀገረ ሰሜን አሜሪካ የሚኖረው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ቁጥሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና በልዩ ልዩ የሥራና የትምህርት ዘርፍ ተሰልፎ አርአያነት ያለው ሥራ እየሰራ ይገኛል። ይህንን መልካም እንቅስቃሴ ለማካፈል ባውዛ ባዜጣችን ከማህበረሰቡ ለማህበረሰቡ በመሆኗ አንጻራዊ በሆነ መልኩ በተሰለፉበት የስራ፣ የቢዝነስ፣ የአገለግሎት ወዘተ የሥራ ዘርፍና መልካምና ረዥም እድሜ የቤተሰብ አኗኗር ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ልምዳቸውን፣ የሕይወት ውጣ ውረዳቸውን አወያይቶና አጠናቅሮ ለንባብ ማቅረቡ ጥሩ ልምድን ወይም ስኬትን ማካፈል ብቻ ሳይሆን ለምን እኔ እንደዚህ ወይም እንደዚያ አላደርግም የሚለውን ጥያቄ የሚጭርና በተቻለ መጠን አላማ ይዞ የተሳካ የሕይወት ጉዞን ለመራመድ እድል ይፈጥራል ብለን እናስባለን። በመሆኑም የቤተሰብንና የቢዝነስ ጉዳዬችን የባውዛ ጋዜጣችን አምዶች በማድረግ አንዱ የማህበረሰባዊ የሥራ ድርሻን ለመወጣት በጠንካራ እንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን።

አንዳንዴ በአስተውሎት ሲያዩት የተለያዩ ሥራዎችን መስራት፣ መልካም ትዳረኝነት፣ ጥሩ የትምህርት ደረጃ ከሁሉም በላይ በሳል አእምሮ፣ ቀና አስተሳሰብና ተግባር እንዲሁም መልካም ባህሪን አጠቃለው የያዙ ግለሰቦችን ስናይ ለነዚህ ሰዎች የተለየ ፕሮግራም (soft-ware) እግዚአብሔር ገጥሞላቸው ይሆን? ወይስ “የጧት እጣ ፈንታ” ማለታችን አይቀሬ ነው። የጋዜጣችን የዝግጅት ክፍል ልክ እንደሁልጊዜው የመወያያ ርዕሶችን በማዘጋጀት የዛሬዋን የቢዝነስና የቤተሰብ (18 ዓመት የቤተሰብ ልምድ) እንግዳ የኢትዮጵያ የሎው ፔጅስ ፕሬዜዳንት ወ/ሮ የሽመቤት በላይ ጋር ያደረግነውን ውይይት እነሆ።



ባውዛ፡- አሁን የደረስሽበት ደረጃ ላይ ሆነሽ ስታይው እዚህ ለመድረስ የሕይወት ፍልስፍናሽ ምን ነበር? ወይም ምንድን ነው?

ወ/ሮ የሺመቤት፡- መጀመሪያ ትልቁ ነገር በሕይወት ስንኖር አቅምንና ጊዜን ሳይቆጥቡ እግዚአብሔር ጤና እስከሰጠ ድርስ መስራት፣ መስራት አሁንም ሳይሰለቹ መስራት፣ እየወደቁ እየተነሱ መስራት የሚል ነው። ሌላው በዚህ የስራ ጉዞና ዘመን በእያንዳንዱ ደቂቃ ለመማር ዝግጁ መሆንና የተማሩትን ተግባራዊ ማድረግ። ከዚያም ወላጅ ለልጆች የመጀመሪያ አስተማሪና መሪ በመሆኑ ስኬትንም ይሁን ውድቀትን ለምን እንደሆነ ለልጆች ማሳወቅ። ይህ ከሆነ ከትናትና ወዲያና ትናንት እንዲህ ወይም እንዲያ ነበረ ዛሬና ነገ የለም ወይም አይታይም የሚለውን የትውልድ ክፍተት እንዳይፈጠር ያግዛል ብዬ አስባለሁ።

በመሆኑም አንድ ቤተሰብ ጥሩ ልጆችን አሳድጎ ለራሳቸውና ለሀገር ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት። ለህብረተሰብ በረከት ማቅረብ ነውና ምንም እንኳን አሜሪካን አገር ስራን እየሰሩ ልጅ ማሳደግ እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም። ከዚህ ጐን ለጐን ሁል ጊዜም ቢሆን መልካም መልካሙን ቀና ቀናውን ማሰብና አካባቢን ወደ ጥሩ ለመቀየር የድርሻን መወጣት “ቸር ተመኝ … ነውና።” መተጋገዝ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በሰው ልጅ ካለ ሁሉንም ነገር ወደጥሩ መቀየር ይቻላል ብዬ አስባለሁ። እናም የእኔ የሕይወት ፍልስፍናዬ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በተሰለፉበት የሥራ መስክ መስራት፣ ከስራና ከህይወት የተማሩትን ለልጆችና ለቤተሰብ ማስተላለፍና በቀናነት በፍቅር በሰላም መኖር የሚል ነው።

ባውዛ፡- ጠቅለል ብሎ ሲታይ የሕይወት ፍልስፍናሽ መስራት የሚቻለውን ያህል በቀናነት መስራትና ኃላፊነትን መወጣት የሚል ነው። ብዙ ጊዜ ብዙ ሰው ላይ ኃላፊነትን (ያለመወጣት) ሳይወጣ ይታያል፤ የቤተሰብ፣ የሥራ፣ የትውልድ የጐረቤት የአካባቢ፣ የመማር ኃላፊነት ሌላም እንዴት እነዚህን ኃላፊነቶች አጣጥሞ መወጣት ይቻላል። በህይወት ውስጥ የተለያዩ ኃላፊነቶች ስላሉ?

ወ/ሮ የሺመቤት፡- ኃላፊነት መወጣትና ስለ ኃላፊነት ለማወቅ ከመጀመሪያው የሕይወት ትምህርት ቤት ከቤተሰብ ነው የሚጀምረው። በተለያየ የእድሜ ደረጃ ሆነህ ወላጆችህ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ሲወጡ ታያለህ። ሌላው ከትምህርት ቤትና ከአካባቢህ የምትማረው ኃላፊነትን የመወጣት እንቅስቃሴ ይኖራል። ስለዚህ አንድ ሰው በልዩ ልዩ የሕይወት እንቅስቃሴው ውስጥ እነዚህን ነጥቦች አገናዝቦ እንደ ቦታውና ጊዜው መስራት የሚገባውን መፈጸም አለበት ብዬ አስባለሁ። ለእኔ የተለያዩ ኃላፊነቶቸን ለመወጣት የጸጸት ቦታ መኖር የለበትም። ትናንትትናና ከትናንትና ወዲያ ለምን እንዲህ አልሆነም ብሎ በጸጸት ፈረስ እየጋለቡ ከመኖር ችግሩን አውቆና ላለመድገም ወስኖ የዛሬን፣ የነገንና ተነገ ወዲያ ያለውንና የሚመጣውን ኃላፊነት ለመወጣት አላማ ይዞ መንቀሳቀስ አግባብነት ይኖረዋል። ባጠቃላይ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ባግባቡ ለመወጣት በተገቢው ጊዜ ተገቢውን ሥራ መስራት ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለኝ።

ባውዛ፡- በተደጋጋሚ ስለ መተጋገዝ ስለ ትውልድ አንስተሻልና እንደ አባባል ይሁን ሌላ ስለ ኢትዮጵውያን ማህበረሰብ ሲነሳ አብሮ መብላት እንጂ አብሮ መስራት፣ መተጋገዝ መደጋገፍ ይጎድለዋል ይባላል። በዚህ ላይ ያንቺ አስተያየት ምንድን ነው። (ከብዙ ሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር ስራሽ ስለሚያገናኝሽ)

ወ/ሮ የሺመቤት፡- እንዳልከው እኔና ባለቤቴ በግል የምናቀሳቅሳቸው ድርጅቶች፣ ኢትዮጵያን የሎው ፔጅስ፣ ባውዛ ጋዜጣ፣ ሊትል ኢትዮጵያ ምግብ ቤት፣ ሊትል ኢትዮጵያ የስጦታ ሱቅና ሌሎች እንቀስቃሴዎች በሰሜን አሜሪካ ካሉ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር ያገናኙኛል። በሰሜን አሜሪካ ረዥም ጊዜ ቆይታየ የተገነዘብሁት ትንሽ የማይባል ኢትዮጵያዊ ይህን አላደረግሁም ወይም አላደረግንም የሚል ይሰማል ወይም አለ። ነገር ግን እኔ እንደማየውና እንደተገነዘብሁት ማን ነውስ አብሮ ጉዳዩን የሚነጋገረው፣ ማን ነውስ የማያውቀው ሰው ቤት ሄዶ የሚያስተዛዝነው፣ ሲታመም የሚጠይቀው፣ ማን ነውስ የማያውቀውን ሬሳ እዚህ አይቀበርም አገሩ ይግባ ብሎ አዋጦ የሚልከው፤ ማን ነውስ ኢትዮጵያ ግሮሰሪ ሄዶ የሚገዛው፣ ኢትዮጵያ ምግብ ቤት ሄዶ የሚመገብ። ባጠቃላይ የአፍ አመል ሆኖ ብዙ ጠንካራ ጎኖች እያሉ አንዷን ትንሽ ነገር አንስቶ አጉልቶ ለማስቀመጥ ካልሆነ መረዳዳቱን፣ መደጋገፍን፣ አብሮ መስራቱን ከኛ የተረፈ ነው ብዬ አስባለሁ።

ባውዛ፡- ወደ ቢዝነስ ሥራ ልመልስሽና በተለይ በአሁኑ ሰዓት ተቀጥሮ ለመስራት እድሉ በጠበበት ወቅት የራስን ቢዝነስ መስራት ብዙ ጠቀሜታ አለው።

ወደ ገጽ 21ይዞራል

## ዜና ንግድ

### “90% የጤፍ እንጀራ”

ድሬ ገበያና ካፌ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ከመቼውም በላይ ተጠናክሮ ደንበኞቹን ለማርካት በዚህ ሀገር የሚመረት 90% የጤፍና ለዲያቤትክስ ህመምተኞች የሚሆን እንጀራ፣ ሁሉን ያካተተ ስቶር፣ ከኢትዮጵያ የሚሰሩ ልዩ ልዩ ብርቅዬ ቁሳቁሶችና ካፍቴሪያ አሟልቶ ሁሉም ሙሉ ሁሉም ዝግጁ እያለ መሆኑን የድርጅቱ ኃላፊ መሰረት ከተማ ለባውዛ ጋዜጣችን ያሳወቁ ሲሆን አድራሻው 4701 North Chambliss St. Alexandria Virginia 22312 ስልክ (703) 942-6673 ነው ብለዋል። የጤፍ እንጀራ ጉዳይ ነውና ቀማምሱት።

### “ጤናችን በጃችን”

ዳይሬክት ሜዲካል አክሰስ በሜዲካል ዶክተር ራሔል ይርጋና በሜዲካል ዶክተር አሽካን ጃፍራቢ ማንኛውም የጤንነት ጥበቃ ምርመራና ህክምና እየሰጠ ሲሆን አድራሻችን 1146 #E Walker Rd, Great Falls, VA 22066 መሆኑን ገልጸዋል። ዋናው ጤና ነውና ጤናን በወቅቱና በተገቢው ቦታ ማግኘቱ አግባብ ነው። ስልክ ቁጥር (703) 438 0720 ማነጋገር ይቻላል።

### “የ138 ዓመት የፋይናንስ እውቀት በአንድ ቀን”

ቢቢ ኤንድ ቲ ባንክ (BB&T Bank) በአቶ ማቴዎስ ቴዎድሮስ የሚንቀሳቀስ የባንክ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሲሆን አድራሻው 1099 New York Avenue, Suite 100, Washington DC ስልክ (202) 347 8079 ወይም በፋክስ (202) 347 4142 ተፈላጊ ኢንፎርሜሽን በነፃ አገልግሎት መጠየቅና ማግኘት የሚቻል መሆኑን ገልጸው የአንድ መቶ ሰላሳ ስምንት አመታት የፋይናንስ እውቀትን በአንድ ቀን ማካፈል ይቻላል ብለዋል። እስትፋሱ ፋይናንስ ነውና አገልግሎቱ ለደንበኞቻችን ይድረሳችሁ ብለናል።

### “ባቅማችን ቤት ለእንግዳ”

ፌር ፋክስ ሪል እስቴት (Fairfax Realty Inc) የቤት ግዢና ሽያጭ በሜሪላንድ፣ ዲሲና ቨርጅንያ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የቤት አማራጮችን በአቅም የሚያቀርብ በመሆኑ ዘመኑ የቤት ነውና በእድሉ ተጠቀሙ እያምልጣችሁ ትላለች ስንዱ ለማ። አድራሻ 1725 Elton Rd. Silver Spring, MD 20903 ስልክ ቁጥር (202) 725-1444 (የእጅ)፣ (301) 439-9500 Ext 3221 የቢሮ መሆኑንና ለብርዱም ለፀሐዩም ከድካም መልስ ለማረፊያ ማን እንደ ቤት ነውና ያማክሩን ያወያዩን። ሳያስቡት የቤት ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉና።

### “በቅልጥፍናችንና በምቾታችን ይመርጡናል”

ቢአርሲ በጀት (BRC BUDGET) የመኪና አከራይና የጉብኝት አገልግሎት ድርጀት ቀልጣፍና ምቾት ያለው መሰተንግዶ ከፈለጉ ሀገር ኢትዮጵያ ጐራ ሲሉ በአገልግሎታችን ይጠቀሙ። የበለጠ ለመረዳት በስልክ ቁጥር 251-911-51-37-08 ደውሎ ማነጋገር የሚቻል መሆኑን ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ አቶ ቢሻው በላይ አሳውቀዋል።

ከገጽ 11 የዞረ

# “ፍቅርና ሰላም ከያዙ…”

ለመሆኑ አንድ ቢዝነስ ከፍቶ ውጤታማ ለመሆን ምን ምን ነገሮች ያስፈልጉታል ብለሽ ታስቢያለሽ?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ የራስን ቢዝነስ ውጤታማ ለማድረግ ብዙ ነገሮች የሚያስፈልጉ ሲሆን እኔ ዋና ዋና የምላቸውን ለመጥቀስ ያህል አንደኛው ጠንክሮ መስራት ነው። ሳይሰለቹ ረዥም ጊዜ ረዥም ሰዓት ሥራው ላይ ማጥፋት ተገቢ ነው። ሌላው አንድ ሰው ሊከፍተው ወይም ሊሰራው ስለአሰበው ቢዝነስ እውቀትና ልምድ ሊኖረው ይገባል። እውቀት ስል ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን ብቻ ሳይሆን ከህይወት፣ ከተግባር ወይም ከብዙ ውጣ ውረድ መማር የበለጠ ብቁ ያደርጋል። አንድን ነገር ከውጪ ሆኖ ማየትና ሥራው ውስጥ ገብቶ መስራትና በተግባር መፈተን በጣም የተለያየ በመሆኑ። ስለዚህ አንድን ቢዝነስ ውጤታማ ለመሆን ተገቢውን ጥናት ማድረግ ምን እንደሚያስፍልግ ማለትም ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል ወዘተ የሚያሳይ ሲሆን የቢዝነስ ፍቅር ደግሞ በቀላሉ መሰላቸትና ተስፋ መቁርጥ እንዳይመጣ ያደርጋል። እኔን በምሳሌነት ብጠቅስ ከሰው ጋር መወያየት፣ መነጋገር እወዳለሁ። እናም የመረጥኩት የቢዝነስ አይነት ከማህበረሰብ ጋር የሚያገኛኝ ነው። እዚህ ላይ መታየት የሚገባው ነጥብ የራስን የሥራ ባህሪ ጠንቅቆ ማወቅና ለዚያ ባህሪ የሚስማማ አይነት ቢዝነስ መክፈት ተገቢ ነው እላለሁ። ባጭሩ ለውጤታማ የቢዝነስ ሥራ የቢዝነሱ ፍቅር፣ አላማና እውቀት ያስፈልጉታል። የቢዝነስ ውድድሩ በጣም እየጠነከር ባለበት ዘመን ሌላው የከፈተውን ቢዝነስ እኔም ልክፈተው ወይም ልስራው ማለት ብዙ ላያዋጣ ይችላል።

ባውዛ፦ አሁን አሁን ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ሁሉንም መሆን ሲፈልጉ ይታያል። ማለትም ሀብታም ሲያዩ ሀብታም፣ የተማረ ሰው ሲያዩ የተማረ ሰው፣ አትሌት ሲያዩ አትሌት፣ እግር ኳስ ተጫዋች ሲያዩ እንደዚያው። ብቻ ሁሉንም ምርጥ ነገር መሞከርና መሆን ባቋራጭ መክበር ይፈልጋሉ በዚህ ላይ ያንቺ አስተያየት ምንድን ነው?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ በመጀመሪያ እውቅናን ስለፈለግነው ብቻ የሚመጣ አይመስለኝም። የሰው ልጅ ታዋቂ የሚሆነው ጠንካራ አስተሳሰብና ለመረጠው ሥራ አትኩሮት ሰጥቶ እዚህም እዚያም ከማለትና ሁሉንም ከመጨበጥ በፍቅርና በጥንካሬ ሲሰራና እግዚአብሔር ሲፈቅደው ነው። ስለዚህ ለእኔ ተገቢ የሚመስለኝ ሁላችንም ፍላጎታችንን፣ ስሜታችንን፣ ችሎታችንን መረዳትና ካሉን ፍላጎትና ችሎታ በመምረጥ ጠንክሮ በመስራት ድክመትንና ጥንካሬን እያዩና እያስተካከሉ በመሄድ ወደሚፈለገው ደረጃ መድረስ ይቻላል።

ባውዛ፦ ከቢዝነስ ሥራ ውጪ ባለቤትሽ አርቲስት ይሁኔ በላይ እውቅ የባህላዊ ሙዚቃ ተጫዋች ነው። ታዲያ ሙዚቃ ከምትሰሪው ቢዝነስ በተጨማሪ ላንቺ እንዴት ይገለጻል?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ ሙዚቃ በተለይም ባህላዊ ሙዚቃ ማለት የአንድን ሀገር ህዝብ ወጉን ልምዱን ማንነቱን፣ ፍቅሩን የሚገለጽበት ነው። ስለዚህ ባህላዊ ሙዚቃ ለእኔ ህይወቴ ነው፤ የማንነቴ መገለጫ ነው፣ ኢትዮጵያዊነቴ ነው ብዬ አስባለሁ። አንድን ሀገር ከምታስተዋውቅባቸው መንገዶች አንዱና ዋናው ባህላዊ ሙዚቃ ነው። እናም ልጆቻችንን ማሳየት የምንፍልገው የሀገራችንን ባህል በተመለከተ ሲሆን የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎችና ባለቤቴ ምርጥ የባህላዊ ሙዚቃ ተጫዎች በመሆኑ ትልቅ ኩራትና ክብር ይሰማኛል። ባለቤቴ ባለው ተሰጥኦ (የኢትዮጵያ የባህል ዘፈኖች) አጠናክሮ እንዲገፋበት እፈልጋለሁ። ባህላዊ ሙዚቃ ለኔ የመንፈስ እርካታዬና የሕይወት ምግቤ ነው።

ባውዛ፦ ባለቤትሽ በሙዚቃ ሕይወት ውስጥ ነው ያለው አንቺ ደግሞ በቢዝነስ ሕይወት ውስጥ ነሽ። ነገር ግን ሙዚቃውና ቢዝነሱ ተጣጥሞ ጥሩና አርአያነት ያለው ቤተሰብ መስርታችኋል። ለመሆኑ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሚስጥሩ ምን ይሆን?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ በቤተሰብ ዙሪያ ከእኔ የበለጠ ለረጅም አመታት በትዳር አለም ላይ የኖሩ ታላቅ ቤተሰቦች ያላቸውን አስተያየትና ልምድ ቢሰጡ ይመረጣል። ነገር ግን ጥያቄው ከቀረበልኝ አይቀር የኔን አስተያየት ለመስጠት በትዳር ላይ ለመጣጣም ትልቁ ነገር መከባበር ነው ብዬ አስባለሁ። እናም ባል ሚስትን ሚስት ባልን ማክበርና ከሁሉም በላይ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ያሉ ባለትዳሮችን ብዙም ባላውቅም ከወላጆቼ የተገነዘብሁት ትልቁ ቁም ነገር መከባበርንና መዋደድን ነው። ያ ለእኔ ትልቁ የትዳር የማዕዘን ድንጋይ ነው። እግዚአብሔርን ተመስገን እለዋለሁ በጣም የምንግባባ ሰዎች ተገናኝተን ጥሩ ትዳር በመመስረታችን። ሌላው እንደሚታወቀው ሁሉ ነገር ባገር ይጣፍጣል። ጋብቻ የምትፈጽመው ቤተሰብ ዘመድ መክሮ ተወያይቶ በመሆኑ። እኛ ግን ተመርጦልን ሳይሆን እኛ ተዋውቀን ተገቢውን ጊዜ ወስደን ተጠናንተን ነው የተጋባነው። ስለዚህ ተዋውቆና ተጠናንቶ ከተጋቡ በኋላ መከባበርና መተማመን ያስፈልጋል ብዬ እላለሁ። የጋብቻ ፊርማ ሳይሆን ለእኔ ትልቁ ነገር የልብ ፊርማ ነው። ስለዚህ ሁሉም ነገር በጋራ ለጋራ መሆን ይገባዋል። ለግል ማሰብ፣ ለግል ትኩረት መስጠት ሊወግድ ይገባል። እናም ለጥሩ ትዳር መሰረቱ መከባበር፣ መተማመንና የእኔነትን ስሜት ማስወገድ ይገባል። ይህ አሁን እየነገርሁህ ያለው የ18 ዓመት የትዳር ሕይወቴን ሲሆን አንድም ቀን ከባለቤቴ ጋር ክፉ ነገር ተነጋግረን አናውቅም እግዚያብሔር ይመስገን። ችግር ካለም ብቻችንን ቁጭ ብለን ተወያይተን እንፈታዋለን። ችግሩም መፍትሄውም ያለው እኛ ዘንድ በመሆኑ። የሚገርመው ነገር አንድ ቀን ቁጭ እንዳልን ልጆችን የተናገረው ነገር አይረሳይኝም። የኔ ወላጆች በጣም የሚገርመኝና የሚያስደስተኝ ነገር አንድም ቀን ሲጨቃጨቁ አላየሁም ነበር ያለው። ስለዚህ ከመጨቃጨቅ ሰከን ብሎ ያለን ችግር ተደማምጦ ለብቻ ጊዜ ወስዶ መፍታት ይገባል። ይህም ሆኖ ትልቁ ነገር እግዚአብሔር ሲጨመርበትና ትዳሩን ሲባርከው ነው የተሳካ ትዳር የሚሆነው።



ባውዛ፦ ትዳረኞች (ባል ወይም ሚስት) አንዳቸው ወይም ሁለቱ ከጋብቻ በፊት የነበራቸው ባህሪ ከጋብቻ በኋላ መቀየር ይታያል። አንዳንዴ የተደበቁ ባህሪዎች ይወጣሉ ይላሉ። መጀመሪያ በጓደኝነት መጠናናቱ እንዳለ ሆኖ። ታዲያ ይህ አይነት የባህሪ ለውጥ ሲያጋጥም ምን መደረግ አለበት ብለሽ ታስቢያለሽ?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ ለትዳር የምታስበውን ሰው መጀመሪያ ጓደኛ በመሆን በደንብ መተዋወቅ መጠናናት ይገባል። ስለዚህ የፈጀውን ጊዜ ወስዶ በደንብ የትዳር ጓደኛን በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል። በጥናቱ ጊዜ ያሉ ልዩነቶችን ለማጥበብና ለመግባባት እንዲቻል መሰራት ያለባቸው ነገሮች ማሟላት ይገባል። በመሆኑም አብዛኛው በጓደኝነት ጊዜ የሚታዩ ልዩነቶች በወቅቱ እየተፈቱ ይሄዳሉ። ከዚያ በኋላ በትዳር ህይወት የሚመጡ ችግሮች በጣም አነስተኛና በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ይሆናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው በችሎታቸው ማድረግ የሚገባቸውን ነገሮች ከማንኛውም ሰው ቅድሚያ ለትዳር በመስጠት መፈጸም አለባቸው። ስለዚህ የቤተሰብ ኃላፊነትን በሚገባ አውቆ ለመወጣት ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ሌላው ከጋብቻ በኋላ ክፍተት የሚፈጥረው ያገቡትን ሰው መጠራጠር ነው። ስለዚህ ከትዳረኛው በላይ ስለእሱ ወይም ስለእሷ የሚያውቅ የለም። ከመጠራጠር ይልቅ ግንኙነትን መፋቀርን ማሻሻል። እናም ትዳር ማለት ነፃነት ማለት እንጂ ባርነት አለመሆኑን ማወቅ። ማድረግ የምትፈልገውን ነገር በግልጽ በመወያየት ማድረግ። እኔና ባለቤቴ የአእምሮና የልብ ነፃነት አለን። ለምሳሌ ባለቤቴ ይህን ማድረግ ሕሌናዬን መንፈሴን ያረካኛል ቢለኝ አእምሮውን የፈቀደውን ነገር (መጥፎ እስካልሆን ድረስ) ማድረግ አለበት። ከተጋቡ፣ ከተዋደዱ በኋላ የት ገባህ የት ወጣህ መባል የለበትም። “እናት አባቱን ይተዋል” ይባል የለ። ባጠቃላይ የሚሰማኝ ለእኔ ሴት ሀይል፣ ሴት ዘዴ ፈጣሪ፣ ሴት ባብዛኛው ጠንቃቃ ስለሆነች ያንን አቅም፣ ያንን ጉልበት ለትዳሯ እንድትጠቀም መቻል አለባት ብዬ አስባለሁ።

ባውዛ፦ የወደፊት ራዕይሽ ( በቤተሰብ፣ በሥራ አካባቢ፣ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ) ምንድን ነው?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ እኔ ቀደም ባሉት ጥያቄዎችህ ላይ መልስ ለመስጠት እንደሞከርሁት በጣም የሚያረካኝ ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፣ መነጋገር መግባባት፣ መተጋገዝ ነው፡፡ ስለዚህም ነው የኢትዮጵያን የሎው ፔጅ ን ማዘጋጀት የጀመርኩት። የኢትዮጵያ የሎው ፔጅ የአንድ ወይም የሁለት ሰው ሳይሆን የሁላችንም ነው። ይህን ካልኩ በኋላ የእኔ ራዕይ በሚመለከት ማንነቴን፣ ሀገሬን የሚያሳይ ሥራ ነው ለመስራት የምፈልገው። እሱ ተዋህዶኛል ማለት እችላላሁ። ውጤቱም የልብ እርካታ ነውና። ስለዚህ አቅሜና ችሎታዬ በፈቀደው መጠን መስራት የምፈልገው የሀገራችንን ባህል የሚያሳይን ከሀገር ጋር የተያያዙ እንዲሆኑ አሁን ካለው የበለጠ ለማድረግ ነው የኔ ምኞት። ልጆቼም የሀገራቸው ጉዳይ በጣም ፍላጎት ስላላቸው ሀገራቸውን የበለጠ እንዲወዱና ለሀገራቸው የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያደርጉ ጥረት አደርጋለሁ።

ባውዛ፦ በትርፍ ጊዜሽ ምን መስራት ትወጃለሽ? ለምን?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ ከቤተሰብ፣ ከልጆቼ ጋር የማሳልፈው ጊዜ የቤተሰብ ሥራ ነው። ከማህበረስቡ ጋር የማደርገው እንቅስቃሴ ሥራ ነው ለእኔ። ስለዚህ ባብዛኛው ጊዜዬን የማሳልፈው በስራ ነው። ነገር ግን አንዳንዴ የሀገር ባህል ሙዚቃ መስማት፣ ማንበብ፣ የአካል እንቅስቃሴ አደርጋለሁ። ባጠቃላይ የኔ የሥራ ባህሪ አብሮ በሄድሁበት ስለሚሄድ እንደሌሎች የቢሮ ስራዎች ቢሮ አስቀምጨው የምመጣው አይደለም። እናም ጊዜየን ከፋፍዬ ይህ የሥራ ጊዜ ይህ የእረፍት ጊዜ ነው ብዬ የማስቀምጠው አይደለም።

ባውዛ፦ መጨረሻ የምታስተላልፊው መልእክት ካለ?

ወ/ሮ የሺመቤት፦ ለወገኖቼ ለኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት የማስተላልፈው መልዕክት የፊታችን ሴፕቴምበር 2011 ለሰባተኛ ጊዜው የኢትዮጵያ ኤክስፖ 2011 በታላቅ ድምቀትና ዝግጅት ይካሄዳል። በዚህ ዝግጅት የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ምርታቸውን እና አገልግሎታቸውን ለተጠቃሚ በሰፊው የሚያስተዋውቁበት ከመሆኑም በላይ በዚህ ዝግጅት የተለያዩና ምርጥ የባህላዊ ዘፈኞች ትርዒት፣ የፋሽን ሾው፣ የታለንት ውድድሮችና የተለያዩ አዝናኝ ዝግጅቶች ይቀርባሉ። በዚህ ታላቅ የኢትዮጵያ ኤክስፖ ላይ በስፖንሰርነትም ሆነ በተለያዩ ዝግጅቶች ለመሳተፍ የምትፈልጉ ድርጅቶች ሆነ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ኤክስፖ ድህረ ገፅ በ www.ethiopianexpo.com በመጐብኘት ወይም በስልክ ቁጥር (202) 387-9302. በመደወል መረጃ ማግኘትም ሆነ መመዝገብ ይቻላል። ይህን ዝግጅት ከቤተሰብ፣ ከጓድኛና ከዘመድ አዝማድ ጋር በመጐብኘትና ለተለያዩ ፕሮግራሞች ተካፋይ በመሆን የማይረሳ ጊዜ ከህዝባችን ጋር እናሳልፍ እያልኩ ጥሪየን በትህትና አቀርባለሁ።

ባውዛ፡ ስለ ሰጡን ቃለ ምልልስ ከልብ እናመሰግናለን።

ወ/ሮ የሺመቤት ፡ እኔም አመሰግናለሁ።